# ALL ETHIOPIA UNITY PARTY (AEUP)
# AUSTRALIA SUPPORT GROUP


**Queensland, Brisbane**
email - meseretbe@hotmail.com.au
Mob - (t) 61 40 248 1218

**Main Office - Perth, Western Australia**
email- mymd@virginbroadband.com.au
Mob- (t) 61 435 469 622

**South Australia, Adelaide**
Mob - Mob- (t) 61 43 235 3301


---

## ሀገራችን ኢትዮጵያን ከውድቀት ለማዳን
## መኢአድን እንደያቅማችን፡ በያለንበት እንደግፍ

ፐርዝ፡ ምዕራብ አውስትራሊያ፡ ሐምሌ 2009

አገራችን ኢትዮጵያ የረጅም ዘመናት የታሪክ ባለቤት የሆነች መሆኑዋ ብቻ ሳይሆን፡ ለሰውልጅ ዘር አመጣጥ የመጀመሪዋ ጥንታዊት አገር ለመሆኑዋ እየተደረጉ ያሉት አለም አቀፍ ሳይንሳዊ ጥናቶች ያረጋገጡት በመሆኑ ለታላቅነትዋ ሌላ ማስረጃ መጥቀስ አስፈላጊ አይመስለንም።

የሚያስገርመው ግን ይደረጋል ብሎ ለማመን ይቅርና ለማሰብ በማይቻልበት ሁኔታ ለአለፉት 18 አመታት አገሪቱ እንደአገር፡ ህዝቡ እንደ ህዝብ፡ በህልውናቸው ለመቀጠል በማይችሉበት የታሪክ አጋጣሚ ላይ መውደቃቸውን በአንክሮ ለተመለከተ ኢትዮጵያዊ፡ ዛሬ በአጎራባች ሱማሊያ ውስጥ የተፈጠረውን እልቂትና ህግ አልባነት ማስታወሱ ተገቢነት ያለው ምሳሌ ነው ብለን እናምናለን። እንደእውነቱ ከሆነ የሱማሊያ ህዝብ የራሱ የሆነ አብሮ የኖረበት የግዛት ክልል የነበረው አንድ አይነት ሃይማኖትና ቋንቋ ያለው ተከባብሮ የኖረ ታላቅ ህዝብ ነበር። ይህንን የተከበረ ህዝብ ተከልለው፡ በውጭ አገራት ጥቅምና ፍላጎት እየተዘወሩ፡ የጎሳ ልዩነትንና አክራሪ አምልኮትን በመስበክ፡ የተለያዩ ቡድኖችን በመፍጠር ተንቀሳቅሰው፡ የሶማሊያን ህዝብ ዛሬ ለደረሰበት መከራ የዳረጉት ጥቂት ቆጠርን፡ ተማርን፡ ሰለጠን፡ የሚሉ የጎሳና የህይማኖት ነፃነትን እናጎናፅፍሃለን ብለው የተነሱ፡ በጎሳ ልዩነት ላይ የተመሰረተ ነፃነት ሰባኪወች ናቸው። በአሁኑ ወቅት ከነዚሁ የጎሳና የአክራሪ እምነት ሰባኪ የጦር አበጋዞች የሱማሊያ ህዝብ ያተረፈው ነገር ቢኖር መብትንና ነፃነትን ሳይሆን እልቂትን፡ ስደትን፡ ህግ አልባነትንና ረሃብን ብቻ ነው። በዚህ ጀብደኝነት ድርጊታቸውም፡ ሶማሊያ የተባለች አገር እንደአገርነትዋ፡ ህዝቡ እንደህዝብነቱ መኖር አለመቻላቸው ብቻ እንዳይበቃ፡ አገሪቷና ህዝቧ የዓለማችን መሳቂያና መዘባበቻ፡ ለአፍሪካም ህዝብ ማፈሪያ ሆነዋል።

አገራችን ታላቋ ኢትዮጵያም በቀጥታም ይሁን በተዛዋሪ ተማርን፡ አወቅን፡ ሰለጠን፡ የሚሉ ምሁራን፡ የጎሳ ጦር አለቃና ልዩነት ሰባኪወች በመሆን፡ የጎሳ የሃይማኖትና የቋንቋን ልዩነት አንደነፃነት በመስበክ፡ ህዝባችንን ያለፈቃዱ ከፋፍለው፡ የተቀጠሩበትን የባእዳን ተልዕኮ ወይም የራሳቸውን የስልጣን ጥም ለመወጣት፡ የሰውዘር መገኛ የሆነችውን ጥንታዊት አገራችንን እያፈረሱና እያስፈረሱ፡ እየገነጠሉና እያስገነጠሉ፡ ህዝባችንን በጅምላ አየገደሉ፡ እያሳደዱ፡ በግዞት እያጎሩ፡ እየዘረፉ፡ በረሃብና በበሽታ እየጨረሱ፡ ግላዊና መንግስታዊ የማምረቻ ተቋዋማትን እያፈረሱ፡ ኢትዮጵያዊነትንና ኢትዮጵያውያንን ሰብዐዊነታቸውንና የህልውና መሰረታቸውን በመፈታተን ላይ ይገኛሉ።

በአሁኑ ወቅት በአገራችን በኢትዮጵያ ውስጥ እየደረሰ ላለው አጠቃላይ ሰብዓዊ ቀውስ ከመጀመሪያውም ጀምሮ በአገራችን ሰሜናዊ የግዛት ክልል ለረጅም አመታት በኤርትራ ክፍለ ሃገራችን ቆላማ ቦታወች መሽገው የኢትዮጵያን ህዝብ ሲገድሉ፡ ሲያስገድሉና ሲዘርፉ የኖሩትና በመጨረሻም ኤርትራን ከእናት



PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

አገሯ ገንጥለው ስልጣን የጨበጡት የአስመራው የጦር አበጋዝ አቶ ኢሳይያስ አፈወርቂና የሚመሩት የጦር ቡድናቸው ለመሆኑ ታሪካችን ምስክር ነው።

አቶ ኢሳይያስ በዚህ ሳይገደቡ በመሃል ኢትዮጵያም የእሳቸውን የቤት ስራ ተቀብሎ ግዳጁን በሚገባ የሚወጣ ጠንካራ የጎሳ ጦር አበጋዝ መሾም ስለነበረባቸው የበኩር ልጃቸውን አቶ መለስ ዜናዊን ሾሙልን። አቶ መለስ ዜናዊ ኢትዮጵያን የማጥፋት ተልዕኮ ተቀብለው የጎሰኝነት ርዕዮትን እየሰበኩና በልዩነት ሳንጃ እየመተሩ ጠንካራ ኢትዮጵያዊነትና ህዝባዊ ፍቅር ያለውን ሁሉ እየገደሉ፡ በአምሳላቸው ጎሰኞችን እየሾሙ በአገራችንና በህዝባችን ላይ ወደር የማይገኝለት የጥፋት ድርጊት በመፈፀም ላይ የሚገኙት ሌላው የትግራይ ነፃ አውጭ የጦር አበጋዝ ለመሆናቸው ለአለፉት 30 ዓመታት የመከራው ቀንበር የተጫነበት ህዝባችን የሚያውቀው በመሆኑ ደግሞ ማስረዳቱ አስፈላጊ አይመስለንም። የሚገርመው ግን እነዚህ ሁለት የጦር አበጋዞች ሌባ ሲሰርቅ ይስማማል፡ ሲካፈል ይጣላል እንደተባለው ሁለቱ በዘረፉት የኢትዮጵያ ሃብት ምክንያት በቀሰቀሱት የጥፋት ጦርነት ያለቀው ህዝባችንና የወደመው ንብረት እንደ ጦርነቱ የጣለው ጠባሳ ሳያገግም፡ አሁንም በድጋሚ ሌላ የጥፋት ጦርነት በህዝባችንና በአገራችን ላይ ለመቀስቀስ በሁሉም ጎን እየተደረገ ያለው ዝግጅትና ኢትዮጵያውያንን በቀጥታም ሆነ በተዛዋሪ የዚሁ ጥፋታቸው ደጋፊና ተባባሪ ለማድረግ የሚያደርጉትን ዝግጅት በፍጥነት ቀጥለውበታል። በሁለቱም ጎንና፡ ሁለቱም ባሰለፏቸው የጥፋት ተባባሪወች የሚደረገውን ዝግጅት በጥንቃቄ ለመረመረ የሚረዳው ሀቅ ቢኖር፡ የጎሳ ጦር አበጋዞችን በመሾምና በመሸለም፡ ሁለቱም ባሰለፉዋቸው የጎሳ ጦር አበጋዞች በመላው አገሪቱ የመጠፋፋትን የጦርነት ችቦ ለመለኮስ መሆኑን ለመገንዘብ ያልቻለ ኢትዮጵያዊ አንድም የነዚህ መሰሪወች ተባባሪ፡ ካልሆነም በሱማሊያ ውስጥ እየተፈፀመ ያለውን ወንጀል በኢትዮጵያም እንዲደገም በናፍቆት የሚጠብቅ ደም የጠማው ግብዝ ብቻ ነው።

እኛ በአውስትራሊያ ሃገር፡ በፐርዝ ከተማ የምንገኝ አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን እናት ሀገራችንና የተከበረው ህዝባችን በአሁኑ ወቅት ያሉበትን ተጨባጭ ሁኔታ በሚገባ መርምረናል። ሰፊ ውይይትም አካሂደንበታል። በተቃውሞው ጎራ የተሰለፉትን የሰላምና የዲሞክራሲ ሃይሎች አገራችንን ከወያኔ ጭቆና ነፃ ለማውጣትና ከጎሳ ፖለቲካ ለማዳን የሚያደርጉትን ጥረት በተለይም የቅንጅትን ጉዞ በጥንቃቄ ስናጠና ቆይተናል። የቅርብ ጊዜ የትግል ተሳትፏችንን ለማስታወስ ያህል፡ እንደ ፈረንጆች አቆጣጠር ጁላይ 27 ቀን 2008 አመታዊ ስብሰባችን ስናካሂድ የስብሰባው ተካፋዮች ሙሉ በሙሉ የተስማማንባቸው ሁለት ግንዛቤወች ነበሩ። አንደኛው፡ የቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ፓርቲ ሀይል መከፋፈል እጅግ በጣም ያሳዘነንና፡ ከምርጫ 97 በፊትም ሆነ ምርጫውን ተከትሎ ትግሉ ያስገኘውን ህዝባዊ ድል ወደ ሁዋላ እንደመለሰውና አቅጣጫ እንዳሳጣው ነው። ከሁሉም በላይ ያሳዘነን የቅንጅት ከፍተኛ አመራር አባላት ከወያኔ ያላግባብ እስራት ከተፈቱ በሗላ የተከሰቱትን አበይት ድርጊቶችን አስመልክቶ፡ በተለይም፡

- *በወያኔ በመጭበርበርም ሆነ በሽማግሌወች ጫና እንደ ጥፋተኛ ሆነው ይቅርታ መጠየቅ፡*
- *ወደ አሜሪካ በሂዱት ልዑካን መካከል የተፈጠረው ችግር፡*
- *የአመራር አባላት ከቅንጅት ተሰንጥቀው ሌሎች ድርጅቶችን መመስረትና*
- *የቅንጅት ስምና አርማው በወያኔ ፍርድ ቤት ውሳኔ መቀማትን፡*

አስመልክቶ በዝርዝር ከፍተኛ ውይይት አድርገንባቸው ነበር፡፡ በመጨረሻም ባለንበት ሆነን የታዘብነው ነገር ቢኖር፡ የትግሉ መሪወች በስምምነት ካፀደቁት የቅንጅት መሰረታዊ አላማ ባይርቁም፡ የባህርይ ግብዝነትና “በስልጡን ፖለቲካ” ካባ የታጀለ ብልጣ ብልጥነት፡ ተጨምሮበት ባጠቃላይ ፖለቲካዊ አለመቻቻል ሀይላቸውን አከፋፍሎ የተጠበቀባቸውን አደራ መወጣት አለመቻላቸውን ነበር።



PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

ከልባችን የምንወደውና ብዙ ተሳትፎ ያደረግንለት ቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ፓርቲ እንደዚህ ስር በሰደደ ሁኔታ መከፋፈሉ ለልባችን ሀዘንና ለአዕምሯችን ጭንቀት ቢጥልብንም፣ ቆራጥና ሀቀኛ የሆኑት ታጋዮች ከስህተታቸው በመማር በዲሞክራሲያዊ ባህርይ የዳበረ፣ ከስትራቴጂና ታክቲክ አንፃር ከበፊቱ የመነጠቀና የበሰለ ድርጅት ስር በመሰለፍና ወገናቸውንም በማሰለፍ የአገራችንና የህዝባችን መብት አስከባሪወችና እንደገናም የምንከራባቸው መሪዎች ይሆናሉ የሚል ተስፋም ነበረን። በወቅቱ ከአንጋፋው መኢአድም ሆነ አዲስ ከተቋቋሙት ድርጅቶች የተሰጡትን መግለጫወችና መልዕክቶች ስንገመግማቸው፣ አሁንም ለኢትዮጵያ ሉዐላዊነትና ለወገናቸው መብት እንደቆሙ፣ ትግላቸውንም በተለያየ ስልት እንደሚቀጥሉ፣ በድርጅቶቹም መካከል ምንም አይነት ቅያሜ እንደሌለና እንዲያውም ከየአንዳንዱ ወደ ሌላው <u>*"የመልካም ዕድል ይግጠማችሁ"*</u> ምኞት እንዳለ ነበር የተገነዘብነው። ነገርግን ብዙም ጊዜ ሳይወስወድ፣ የድርጅቶቹና ይዘትና የመሪወቹ ሰትራቴጂካዊ አመለካከት በፍጥነት መልኩን ቀየረ።

ከላይ የጠቀስናቸው ችግሮች ያስከተሉትን የቅንጅትን መፈረካከስ በጥርዝ ኗሪ የሆንነውን ኢትዮጵያውያን የአላማ አንድነታችን እንዳይመርዘው ከመስጋታችን የተነሳ መኢአድንም ሆነ በአዲስ የተቋቋሙትን ድርጅቶች፣ ሁሉንም በእኩልነት በመመልከት በየዘርፋቸው ለሚያካሂዱት ቆራጥ ትግል ድጋፋችንን ለመስጠትና የሁሉንም ስራና ሂደት በጥሞና ለመከታተል በመወሰን፣ ይህንኑ የፀና አቋማችንን ለክቡር ኤንጂኔር ሃይሉ ሻውል፣ ለክብርት ወ/ት ብርቱካን ሚዴቅሳ፣ ለክቡር ዶክተር ብርሃኑ ነጋና ለኢትዮጵያዊ ኤሌክትሮኒክ ሚዲያወች በሙሉ እንዳስተላለፍን የሚታወስ ከመሆኑም በላይ ድርጅቶቹም ላስተላለፍንላቸው መልዕክት በአክብሮት ማብራሪያ እንደሰጡን በዚህ አጋጣሚ ልንገልፅ እንወዳለን።

በፖለቲካ ዓለም 15 ደቂቃ ረዥም ነው እንደተባለው፣ እኛም አንድ አመት ባልሞላ ጊዜ ከላይ የዘረዘርነውን አቋማችንን እንድናስተካክል ተገደናል። የሃገራችንን የፖለቲካ፣ ኤኮኖሚና ማህበራዊ ተጨባጭ ሁኔታ በመገንዘብ፣ የኛም ተሳትፎ በምን መልክ መሆን እንዳለበትና፣ የበኩላችን ዘላቂ አስተዋፅዖ ለማድረግ፣ በህዝባችንና በአገራችን ላይ በጠላትነት የተሰለፉትን ሃይሎችና ተባባሪወቻቸውን ለይቶ ማወቅ አስፈላጊ በመሆኑ ጉዳዩን በጥንቃቄ መረምረናል።

እንደሚታወቀው የኢትዮጵያ የፖለቲካ ሁኔታ በፍጥነት በመቀያየር ላይ እንደሆነና በተለይም በፖለቲካው አንጻር ተቃዋሚ ድርጅቶች መፈናፈኛ በማጣት፣ አባሎቻቸው ለሞት፣ ለእስርና ለስደት በመዳረግ ላይ እንደሚገኙ ከሁላችንም የተሰወረ አይደለም። ቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ፓርቲ ውስጣዊ በሆኑ ታክቲካዊ ችግሮችና ውጫዊ በሆነ ጠንካራ የጠላት ስራ ሃይሉ ተበታትኖ፣ አብዛኛው አባላቱም ወደ አንጋፋው ድርጅታቸው ወደ መላ ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት ሲመለሱ፣ የቀሩት ደግሞ አንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲና፣ ግንቦት 7 ንቅናቄ የሚባሉ ድርጅቶችን መስርተዋል። ከቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ፓርቲ ፍልስፍና ሶስት መሰረታዊ ምሰሶወች ተጨምቀው ሊወጡ እንደሚችሉ እናውቃለን። እነኝህም፣

1. ኢትዮጵያዊነት ህብረ ብሔርነት ነው። የሀገሪቷ ዳር ድንበርና ነጻነት፣ የህዝቧም አንድነት ተጠብቆ የኖረው በዚህ ህብረ-ብሄራዊ በሆነ ተፈጥሯዊና ጠንካራ ቁርኝት ነው።
2. የግለ ሰብ መብት ከተከበረ የብሄርም ሆነ የህብረ ብሄር ፡ ወይም የጎሳ መብት ተከበረ ማለት ነው። የብሄርም ሆነ የህብረ ብሄር ድርጅቶች አባላቱ ግለ ሰቦች ናቸውና። በዘር ወይም ብሄር ፖለቲካ መደራጀት ህዘቡን ይበታትናል፣ ይከፋፍላል። የተለያዩ ብሄሮች ተወላጆች ተሰባጥረውና ተፈጥሯዊ ቁርኝት አድርገው በሚኖሩባት ሀገር፣ ያላቸው ችግርና ብሶት የጋራ ነውና፣ ትግሉም የሁሉንም ብሄርም ሆነ ብሄረ-ሰብ አባላት ወንድማዊ ትብብር የሚጠይቅ ነው ። ይህ ሲሆን ብቻ ነው ሁሉም ዜጋ በአሸናፊነት መብቱን ሊቀዳጅ የሚችለው።
3. ዳር ድምበራችንና አንድነታችንን ጠብቀን፣ ይህን ሀገር አቀፍ ብሶትና ችግር ለማስወገድ፣ የህግ የበላይነት የሰፈነበትና የዜጎች እኩልነት መብት የተረጋገጠበት መልካም አስተዳደር ለመመስረት የምናደርገው ትግል ዲሞክራሲያዊና ሰላማዊ መሆን አለበት የሚሉት ናቸው።

እነዚን ሶስት መሰረታዊ የፍልስፍና ምሰሶወች ይዘው ሊቀጥሉ የሚችሉ የፖለቲካ ፓርቲወች መላ ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅትና፣ አንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ ብቻ መሆናቸውም ግምት ውስጥ


PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

አስገብተን ነበር። ምክንያቱም የግንቦት 7 ንቅናቄ የትግል ስልት ከቀድሞው የቅንጅት ፍልስፍና፣ በተለይም ትግሉ ዲሞክራሲያዊና ሰላማዊ መሆን አለበት ሲባል ከነበርው መሪ ሃሳብ በመውጣቱ ነው።

መላ ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅትና፣ አንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ አሁን ትግላቸውን በየበኩላቸው ቀጥለዋል። አንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ በአሁኑ አቋሙ የትግል አጋር አድርጎ ከተመዘገበበት መድረክ ከተባለው ስብስብ ውስጥ 90 በመቶው በዘርና በጎሳ ከተደራጁ፣ አስገንጣይና ተገንጣይ፣ ፀረ-ኢትዮጵያ፣ ፀረ-አንድነት፣ ፀረ-ታሪክና ኢትዮጵያዊነት በሆኑ አፍራሽ የፖለቲካ መርሆወች የተደራጁ መሆናቸው ግልፅ ነው። ለምን ብንል የመድረክ አባላት እንደሚከተለው በመሆናቸው ነው። አረና ትግራይ፣ ኦሮሞ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ንቅናቄ፣ ሶማሌ ዲሞክራሲያዊ አንድነት ግንባር፣ ኦሮሞ ህዝባዊ ኮንግሬስ፣ የደቡብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ዲሞክራሲያዊ ኮንግሬስና ህብረ ብሄራዊ ሽፋን ለመስጠት ደግሞ የአንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲና የኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ አንድነት ንቅናቄ በተለጣፊነት ይገኙበታል።

ከላይ የተዘረዘሩትን የፖለቲካ ፓርቲወች ስር መሰረትና፣ በተለይም ልሂቃን መሪወቻቸው እስከዛሬ ድረስ የኢትዮጵያ ህዝብ የሃገሩን ሉዓላዊነትና የራሱን ሰብዓዊና ፖለቲካዊ መብት ለማስከበር በሚያደርገው መራራ ትግል የተጫወቱት ሚና ምን እንደነበር በጥልቅ ለመመርመር ይህ መግለጫ ባይፈቅድም፣ በመድረክ ቁንጮ ላይ የተቀመጡትና ዛሬ እኛ ብቻ ነን ዲሞክራሲን ለኢትዮጵያ ማምጣት የምንችለው እያሉ የሚፎክሩት ተዋናዮች፣ የኢትዮጵያ ሉዓላዊነትም ሆነ የህዝቧን ሰብዓዊና ፖለቲካዊ መብት ያፈረሱ፣ እጃቸው በደም የተጨማለቀ ወንጀለኞች መሆናቸውን የቅርብ ታሪካችን ይመሰክራል።

ከላይ የተዘረዘሩት የመድረክ ፀናሾችና አርኪቴክቶች መላ ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት እንዲቀላቀላቸውና አብሮ እንዲሰራ ሲጠይቁት፣ እምቢ ከማለት ይልቅ የሚከተሉትን ግልፅና ቁልፍ ጥያቄወች አቅርቧል።

1. የመድረክ አላማና ግብ ምንድን ነው?
2. በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፓብሊክ ህገ መንግስት አንቀፅ 39 ላይ መድረክ ያለው አቋም ምንድን ነው?
3. የተለያዩ ጎሳወች በተናጠል በፖለቲካ ስለመደራጀት መድረክ ያለው አቋም ምንድን ነው?
4. በኢትዮጵያ ሉዓላዊነት መከበር መድረክ ያለው አቋም ምንድን ነው?

የሚሉት ሲሆኑ ለነኝህ ግልፅና ቁልፍ ጥያቄወችም አጥጋቢ መልስ ባለማግኘቱ ወይም የተሰጠው መልስ ለሃገራችን ደህንነትና ለህዝባችን አንድነት ይበጃል ብሎ ስላላመነበት የመኢአድ ከፍተኛ አመራር የመድረክን እንቀላቀል ግብዣ በአሉታ መመለሱን ሁላችንም እናውቃለን። በዚህ አጋጣሚ ለህዝባቸውና ለአገራቸው ህልውና የገቡትን ቃል ሳያጥፉ ክቡር መስዋዕትነት የከፈሉትና በመክፈል ላይ ለሚገኙት የመኢአድ አባላትና አመራር ለመልካም ስራቸው ምስጋናችንን እናቀርባለን።

ዛሬ አገራችን ካለችበት ችግር ነፃ ሊያወጣ የሚችልና የራሱን የፖለቲካ ፕሮግራም ይዞ የሚንቀሳቀስ አንጋፋ ድርጅት ቢኖር መላ ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (መ ኢ. አ ድ) ብቻ ነው። እኛም ባለንበት ያለችንን ገንዘብና ጊዜ በትክክል ለትግሉ እናበርክት የምንል ከሆነ፣ ***በሃገራችን ነፃና ገለልተኛ ምርጫ እንዲካሄድ፣ የህዝባችን ሰብዓዊና ፖለቲካዊ መብቶች እንዲከበሩ፣ ህግ የሁሉም የበላይ እንዲሆን፣ የዳኝነቱ ስርዓት ከፖለቲካ ተፅዕኖ ነጻ እንዲሆን፣ የመንግስት ሰራተኞችና መለዮ ለባሹ ከዘር አደረጃጀትና ከፖለቲካ ሽኩቻ ገለልተኛ ሆነው የሁሉም አገልጋይ እንዲሆኑ፣*** የሚሉትን መሰረታዊ ህዝባዊ ጥያቄወችን መርሆው አድርጎ፣ ከህዝባችን መሃል ሆኖ ሰላማዊና ዲሞክራሲያዊ ትግሉን እያካሄደ ያለው መላ ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት ለመሆኑ ከሚያሳየን ተግባራዊ እንቅስቃሴ ውጭ ሌላ መመዘኛ ማውጣት የሚቻል አይሁንም። በመሆኑም ኢትዮጵያን የሚወድ ኢትዮጵያዊ መኢአድን የማጠናከርና የመርዳት ኢትዮያዊ ግዴታ አለበት እንላለን ።

ስለዚህ በሚከተሉት ነጥቦች ላይ በማተኮር፣ በውጭ ሀገር ለሚኖሩ፣ አገራቸውንና ወገናቸውን ከልብ እንወዳለን ለሚሉ ኢትዮጵያውያን፣ ጉዳዩ በቀጥታ ይመለከተናል ለሚሉ ምሁራንና አገራችንን ከውድቀት ለማዳን ለሚያስቡ ሁሉ የሚከተለውን መልዕክትና ጥሪ እናስተላልፋለን።



PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

1ኛ. በአሁኑ ወቅት በስልጣን ላይ ከሚገኘው እራሱን የትግራይ ነፃ አውጭ ድርጅት ብሎ ከሚጠራው ቡድን በተጨማሪ በቅርብ ጊዜ የተከሰተ አረና ትግራይ የሚባል የፖለቲካ ድርጅት እንዳለ ግልፅ ነው። ሁለቱም ድርጅቶች ለትግራይ ህዝብ ታማኝ፡ አሳቢና ተቆርቋሪ በመምሰል ለዳግም ጥፋት በየፊናቸው፡ በስውርም ሆነ በግልፅ የየራሳቸውን እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ ይገኛሉ። በትግርኛ ተናጋሪውም ሆነ በሌላው ህዝባችን ላይ ለአለፉት 30 ዓመታት የሚፈፀመውን ግፍ በጥንቃቄ ለሚመለከት፡ ህገ ወጥ ግድያን፡ የሃገር ሃብት ምዝበራን፡ ፖለቲካዊ ማጭበርበርን፡ ጎሳዊ ግለኝነትን፡ ታሪካዊ ክህደትን፡ የዘር ጥላቻንና ሙስናን ወያኔና ግብረ አበሮቹ የህልውናቸው መሰረትና የስልጣን ጊዜ ማራዘሚያ አድርገው የሚጠቀሙባቸው አይነተኛ መሳሪያወቻቸውና ስልታቸው መሆናቸው የታወቀ ነው። የትግራይ ህዝብ ህገ ወጥ ግድያን፡ የሃገር ሃብት ምዝበራን፡ ፖለቲካዊ ማጭበርበርን፡ ጎሳዊ ግለኝነትን፡ ታሪካዊ ክህደትን፡ የዘር ጥላቻንና ሙስናን እንደማይቀበል ግልፅ ነው። የትግራይ ህዝብ ለሃገሩ፡ ላንድነቱና ለሰንደቅ ዓላማው ሞቷል። የአገሩን መገነጣጠልም ሆነ የህዝቡን መበታተን አይፈቅድም። ህገ ወጥ ግድያ፡ የሃገር ሃብት ምዝበራ፡ ፖለቲካዊ ማጭበርበር፡ ጎሳዊ ግለኝነት፡ ታሪካዊ ክህደት፡ የዘር ጥላቻና ሙስና ወንጀል እንጂ የነፃነት ዋጋ አለመሆናቸውን ጠንቅቆ ያውቃል። የትግራይ ህዝብ በተፈጥሮውና በደም ትስስሩ በኢትዮጵያዊነቱ የሚኮራ እንጅ በዝቅተኝነት መንፈስ የሚያብድ አይደለም። ባጭሩ የትግራይ መኢአድ አባላትና አመራር አካላት ህዝቡ የሚኖረውን መከራና ስቃይ አብረው እየገፉ ለነጻነታችን ለባንዲራችን፡ በጠቅላላው ለኢትዮጵያ ህልውና የሚያደርጉትን መራራ ትግል ከልብ እያደነቅን ሰውበላው ወያኔ በትግራይ መኢአድ ጽ/ቤት በአመራር አባላትና በደጋፊው ህዝብ ላይ የሚፈዕመውን ልዩ ግፍ እናወግዛለን።

2ኛ. የኤርትራው መሪ አቶ ኢሳኢይስ አፈወርቂ "እንደ ሲንጋፖር ደሴት የሰለጠነች" ሊያደርጓት የገነጠሏትን አገረ ኤርትራ ከመምራት ውጭ በኢትዮጵያ ጉዳይ ጣልቃ በመግባት የአገራችንን ሰላምና ደህንነት ለማናጋት የሚያደርጉት ሴራ ከባድ ችግር ፈጥሯል። ችግሩ ዘላቂ ፍትህ እስካላገኘ ድረስ ወደፊትም ችግር ይፈጥራል። በአቶ ኢሳኢያስ አፈወርቂ መልካም ፈቃድና ድርጅታዊ ድጋፍ ሃገራችን ዲሞክራሲያዊ ስርዐትና መልካም አገዛዝ ትጎናፀፋለች ብለው የሚሰብኩን ሁሉ የቅርብ ጊዜውን የኢትዮጵያንና የኤርትራን ታሪክ በትክክል ያልተገነዘቡ ናቸው። ወይም ከአቶ ኢሳይያስ አፈወርቂ የጦር አበጋዝነት ሹመት ለመቀበልና አገራቸውን እንደሱማሊያ የዘር ጦርነት እሳት ሊያነዱባት የተዘጋጁ ናቸው።

3ኛ. ከምርጫ 97 ወዲህ ያለውን የተቃዋሚ ሃይሎችን አሰላለፍና እንቅስቃሴ በሚገባ ገምግመናል። በርካታ መረጃወችንም አገላብጠናል። በአገር ውስጥ ያለውን በተለይም የልብ ትርታ ከሩቅ ሆነን በሚገባ አድምጠናል። ዛሬ በተቃውሞ ስም ሁሉም የቀድሞውን የቅንጅትን መንፈስና ዓላማ ይከተላሉ ለማለት አይቻልም። በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንደተባለው በወያኔ/ኢህአዴግ የሚሰነዘረው ግፍና ጭፍጨፋ የማይበቃ ይመስል፡ አንዳንዶቹም የቅንጅትን መንፈስ አንዴ በቆረጣ፡ አለያም በለበጣ፡ ህዝቡ የከፈለውን ክቡር መስዋዕትነት ወደ ጎን በማሽቀንጠር፡ ወደዱሮው፡ ወደሚከረፋውና ጥለነው መጣን ወዳልነው የጎሳና ጠባብ ፖለቲካ ክምችትና አስተሳሰብ ተመልሰዋል። መኢአድ ግን ለህዝቡ የገባውን ቃል ሳይጥፍ፡ የቅንጅትን መንፈስና ዓላማ ሳይቀይር፡ አባላቱም በወያኔ ዘረኛ ወታደሮችና ታጣቂወች፡ በፍርደ ገምድል ዳኞችና የህግ ተቋማት የተቃጣባቸውን መከራና ስቃይ ከወገናችው ጋር ሆነው በመቋቋም ሰላማዊ ትግሉን በመቀጠል ድርጅቱም ሆነ አመራሩ ህዝባዊ ታማኝነቱን አረጋግጧል። ከአስመሳይ ተቃዋሚነት የፀዳና፡ በስልጣን ላይ ላለው ገዥ ቡድን የህቡዕም ሆነ ግልፅ አጋርነት የሌለው፡ እውነተኛ፡ ህዝባዊ ሲቪል የፖለቲካ ድርጅት መሆኑን በተግባሩ አስመስክሯል። ስለዚህ ሊደገፍ የሚገባው ድርጅት እናምናለን።

4ኛ. ማንኛችንም ለአገራችንና ለህዝባችንን የምንቆረቆር ምሁራን፡ የአገር ሽማግሌ፡ የሃይማኖት አባቶች፡ በውስጥም ሆነ በውጭ የምንገኝ ኢትዮጵያውያን ሁሉ ባሳለፍናቸው 30 ዓመታት ውስጥ



PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

የተማርነው የትግል ታሪክ ቢኖር የጎሳ ጦርነትና የጎሳ ፖለቲካ ማንንም ከጭቆና ነፃ እንዳላወጣ ነው። ጊዜአዊ አሸናፊነትን የተቀዳጁት አቶ መለስና የጎሳ ሹሞቻቸውም የአዕምሮ ነጻነት የሌላቸውና በሃገርም ውስጥ ሆነ በውጭ ሀገር ተዘዋውረው በወገናቸው ፊት እንኳን ለመቆም ከባድ የጥበቃ ሃይል ያሰፈልጋቸዋል። ማንንም ከማን ነፃ የሚያወጣም ሆነ፣ ነፃ የሚወጣ ስለሌለ የዚህና የዚያ ጎሳ ነፃ አውጭ ድርጅት በመባል የምትታወቁት ሁሉ፣ ይህን አፍራሽ አስተሳሰብ ትታችሁ፣ ሁላችሁም የአገራችንን ችግር በወንድማማችነት፣ በመተሳሰብና በሰላማዊ መንገድ እንድትፈቱ አጥብቀን እናሳስባለን።

5ኛ. በተለይም በውጭ ደልቶን የምንኖረውና የወገናችን መራራ ትግል አጋር ነን የምንል ሁሉ፣ በዚህ ትግል ዙሪያ የሚኖረንን አስተዋፅኦና ሚና በትክክል መረዳት ይኖርብናል። ትግሉን የሚያካሂዱት መሪወች የሚኖሩት በምዕራብ ዓለም ዋና ከተሞች መሀል ሳይሆን፣ በሀገራቸው ውስጥ፣ በወገኖቻቸው መሃል በመሆንና፣ የሃገሪቱንና የዜጎቿን የልብ ትርታ አብሮ በማዳመጥ፣ ችግሩን በመካፈልና ታላቅ የኑሮ መስዋዕትነትን በመክፈል ነው። የኛም አስተዋፅኦ መሆን ያለበት ትግሉና ታጋዮቹ የሚያስፈልጋቸውን የሞራል፣ የቁሳቁስና የዲፕሎማሲያዊ የማያቋርጥ ዕርዳታ ማበርከት ነው። ምን ጊዜም ቢሆን ከአዕምሯችን መጥፋት የሌለበት አወንታ ቢኖር፣ ወያኔ በስልጣን ለመቆየት የሀገራችንን ፖለቲካዊ፣ ወታደራዊና ኤኮኖሚያዊ መዋቅሮችንና አውታሮችን በሙሉ በቁጥጥሩ ስር በማድረግ ብቸኛ ተጠቃሚ መሆኑንና፣ ባንፃሩ ደግሞ ያለደሞዝና አበል ክፍያ፣ በኢትዮጵያዊነት ወኔ ብቻ ከፍተኛ የህይወት የገንዘብ የጊዜ መስዋዕትነትን እያደረጉ፣ መራራውን ትግል አመራር በመስጠት ላሉት አባቶቻችን፣ እናቶቻችን፣ ወንድሞቻችችንና እህቶቻችን ያለናቸው አለኝታ እኛ በድሎት በውጭ ሀገር የምኖነረው ኢትዮጵያውያን መሆናችን አውቀን፣ ትግሉ ባስቸኳይ ድል እንዲቀዳጅ የምንፈልግ ከሆነ፣ ቀጣይ የሆነ የማቴሪያል ዕርዳታ የማድረግ ግዳጅና ሃላፊነት እንዳለብን አጥብቀን እናሳስባለን።

6ኛ. ባሁኑ የመጨረሻ ሰዓት እየተካሄደ ያለውን መራራ ዲሞክራሲያዊና ሰላማዊ ትግላችን በግንባር ቀደምትነት እየመራ ያለውና ዕውነተኛም ህብረ ብሄራዊ የሆነው ድርጅት መኢአድ ብቻ በመሆኑ በያላችሁበት ለድርጅቶች ደጋፊ መሆን ያልፈለጋችሁ ሁሉ፣ በዕውነት የትግሉ አጋር ነን እስካላችሁ ድረስ የመኢአድ ተባባሪ መሆን የማትችሉበት ምክንያት አይታየንም። ለመኢአድ በፖለቲካ ድርጅትነቱ አማራውን ህዝብ ብቻ ይወክላል በማለት መቀነቱ ጠለፈኝ ሰበብ ለምታላዝኑት ሁሉ፣ የመኢአድ ከፍተኛ አመራር አባላት የተሰባጠሩ፣ ከምስራቅ እስከ ምዕራብ፣ ከሰሜን እስከ ደቡብ ኢትዮጵያን የሚወክሉ ዕውነተኛ ህብረ ብሄራዊ ስብስብ መሆናቸው ከራሳችው አንደበት በተደጋጋሚ የተነገረ ስለሆነ እዚህ ላይ መድገም አስፈላጊ አልነበረም፡፡ አመራሩ ከአማራ ህዝብ ብቻ እንኳን ቢወጣም እኛ ጉዳያችን ከመልዕክቱ ምንነት እንጅ ከመልዕክተኛው ማንነት መሆንም የለበትም። በተጨማሪም በእያንዳንዱ ብሄር ብሄረ-ስብ ለሀገሩና ለወገኑ ደህንነት የተሰለፈ እንዳለ ሁሉ፣ ሃገሩንና ወገኑንም እያጠፋ ያለው ወያኔ/ኢህአዴግ ብሎ ራሱን የሰየመው ድርጅትም መሪወች የተውጣጡት ከሁሉም ብሄር ብሄረ-ሰብ እንደሆኑ ግልፅ ነው። ስለዚህ፣ ምክንያት ማብዛቱ ይቁምና፣ ሁላችንም የመኢአድ የድጋፍ ማህበር አባል ወየም ተባባሪ በመሆን ትግላችንን በያለንበት እናፋፍም።

7ኛ. መኢአድን ላለመደገፍ ከሚቀርቡ ምክንያቶች አንዱ ደግሞ ድርጅታዊ ስራና ፕሮሲጀር ድክመት እንዳለ የሚጠቁም ነው። የአንድ ፖለቲካ ድርጅት ጥራቱ የሚለካው በፖሊሲውና ያን ፖሊሲ በሚያስፈፅምበት መንገድ ስለሆነ፣ ትችቱ አግባብ ያለውና በመረጃ የተደገፈ እስከሆነ ድረስ፣ ትችት መኖር የለበትም የሚል ማንም የለም። ከደርግ ኢትዮጵያ ሰራተኞች ፓርቲ ጀምሮ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በሃገራችን የታየውን የፖለቲካ ፓርቲወች የስራ ልምድ ብንመረምር አንድም ፓርቲ ፍፁም ትክክለኛና ስህተት አልባ ነው ለማለት የምንችል አይመስለንም። የሃገራችንና የህዝባችን ችግራችንም የፖለቲካ ፓርቲወች የፕሮሲጀር ስህተት ሳይሆን፣ ዳር ድምበር የገረሰሰው፣ ኤርትራን ያሰገነጠለው፣ ሀገሪቱን በማይረባ ጎሳዊ ክልል መንግስት የከፋፈለው፣ የሀገር ተቋማትን በሙሉ



PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

አፍርሶ ወገናችንን ለስደት የዳረገው፡ ብዙ ህይወት ያጠፋው የወያኔ/ኢ.ህአዴግ መንግስት መሆኑን አንርሳ።

ኢ.ትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!
ከመኢ.አድ ጋር ወደፊት!



PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com